## ምድብ ሁለት (ከ1ኛ-3ኛ ክፍል)

## 31ኛ ሳምንት

## ዕርገት

**ዓላማ**

❖ የክርስቶስ ዕርገት ታሪክ መማር፡፡

**ምንባብ**

❖ ማር.16÷14-20

**መግቢያ**

❖ በዛሬው ትምህርታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ መቼ እንዳረገ፣የት እንዳረገ፣ከማረጉ በፊት ለደዘመዛሙርቱ ምን እንዳስተማራቸው፣ደቀመዛሙርቱ ወደ ዐረገበት አንገጠው እያሉ መላእክቱ ምን እንደነገሩዋቸው እንማራለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ከጌታ ቃል የተሰቀሉ ሰዎች ስንት ናቸው?ለምንስ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው?
2. በመስቀል ላይ ምህረት የጠየቀው ማነው? ምን አገኘስ?
3. አይሁድ ሲሰድቡትና ሲሰቅሉት ክርስቶስ ምን አደረገ?

**ትምህርቱ**

❖ ጌታችን ከሞት ከተነሳ በኋላ በተለያየ ቦታ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ እየተገለጠ 40 ቀንና ሌሊት ቆየ፡፡

❖ ብዙ ታዓምራት እያሳያቸው እና እያስተማራቸው አዕምሮአቸውን ከፈተላቸው "ስለዚህም የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጎሜና ስለርሱ የተነገራቸውን አስተዋሉ፡፡" ወደ ዓለም ወጥተው አህዛብን በሙሉ ወንጌል እንዲያስተምሩ አዘዛቸው፡፡

❖ የሚያምኑት ብዙ ታዓምራትን ምልክቶች እንደሚከተሉዋቸው አጋንንት እንደሚያወጡ፣በሽተኞችን እንደሚፈውሱ ሌሎችም ብዙ ተዓምራት እንደሚፈጽሙ ነገራቸው፡፡

❖ ከዚያም እየባረካቸው ወደ ሰማይ ከፍ አለ፡፡ደመናም ጋረደው፡፡ከዓይናቸው ተሰወረባቸው፡፡

❖ ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው ***"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው፡፡"***

❖ ደቀመዛሙርቱም ጌታ ካረገበት ከደብረዘይት እግዚአብሔርን እያከበሩ ተመለሱ፡፡

**መዝሙር**፡-

ሞትን ድል አድርጎ የተነሳው ጌታ (2)
ዐረገ(2) በእልልታ (4)

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ጌታ ከተነሳ ከ __________________ ቀናት በኋላ ዐረገ፡፡
2. ሐዋርያት መጻሕፍት ያስተዋሉት ጌታ ________________ ሲከፍትላቸው ነው፡፡
3. የማያምኑትን ብዙ ______________ ይከተሉቸዋል፡፡ ሲል ጌታችን አስተማረ፡፡

ይቆየን....

**አዘጋጅ፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ** **ግንቦት ፯ ቀን ፪፻፪ ዓ.ም**